በህይወታችን ዙሪያ ልንላቸው የሚገቡ ዚክሮች እና ዱአዎች

በቀይ የሚፃፉት ዚክሮች እና ዱአዎች ሲሆኑ በ ጥቁር የተፃፉት ደሞ የዚክሮቹ እና የዱአዎቹ ጥቅሞች እና ማብራሪያዎች ናቸው

◆ አላሁመ ኢኒ ኡሽሂዱከ ወኡሽሂዱ መላኢከተከ ወሀመለተ አርሺክ ወኡሽሂዱ መንፊሰማዋቲ ወመን ፊልአርዲ አነሁ አንተላሁ ላኢላሀ ኢላ አንት ወሀደከ ላሸሪከለክ ወአሽሀዱ አነ ሙሀመደን አብዱከ ወረሱሉክ

➥ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል ይህንን ዚክር 1 ጊዜ ያለ አላህ(ሱ.ወ) የአካሉን አንድ ሶስተኛ ከእሳት ነፃ ይልለታል 2 ጊዜ ያለ የአካሉን ሁለት ሶስተኛ ነፃ ይልለታል በብዛት ካልነው ከእሳት እራሳችንን እንጠብቃለን ማለት ነው

◆ አልሀምዱሊላሂ ለዚ አጥኣመኒ ሀዘ ጧአመ ሚን ገይሪ ሀውሊን ሚኒ ወላ ቁዋ

➥ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል ይህን ዚክር ምግብ በልተን ከጨረስን በኋላ ካልን ከፊለፊት ያለውን ወንጀላችንን አላህ(ሱ.ወ) ይምርልናል(ወደ ፊት የምንሰራው ወንጀላችን ይማርልናል)

◆አሽሀዱ አንላኢላሀ ኢለላህ ወሀደሁ ላሸሪከለህ ወአሽሀዱ አነ ሙሀመደን አብዱሁ ወረሱሉህ

➥ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል አንድ ሰው ውዱእ ካደረገ በኋላ ይህንን ዚክር ካለ ስምንቱም የጀነት በር ተከፍተውለት በፈለከው ግባ ይባላል

◆ላኢላህ ኢለላህ ወሀደሁ ላ ሸሪከለህ ለሁል ሙልኩ ወለሁል አምድ ወሁወ አላኩሊ ሸይኢን ቀዲር

➥ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል ይህንን ዚክር 100 ጊዜ ያለ 5 ሸልማት አለው 1,መቶ አጅር ያገኛል 2,መቶ ወንጀል ይማርለታል 3,አስር የኢስማኢልን ልጆች ሁር እንዳለ ይቆጠርለታል 4,በዛን ቀን ከሸይጣን የተጠበቀ ነው 5,የውመል ቂያሚ እንደሱ ማንም አጅር ይዞ አይመጣም እንደሱ ያለ ወይም ከሱ በላይ ይህን ዚክር ያለ ሲቀር

◆ሱብሀነላህ ወቢሀምዲህ ሱብሀነላሂል አዚም

➥ ይህ ዚክር ምላስ ላይ ቀላል የፍርዱ ቀን ሚዛን ላይ ከባድ አላህ(ሱ.ወ) ዘንድ በጣም ተወዳጅ ይህን ዚክር 1 ጊዜ ያለ በጀነት ውስጥ 1 የተምር ዛፍ ይተከልለታል 1000 ጊዜ ካለ 1000 የተምር ዛፍ ይተከልለታል እና ታዲያ ይህ ዚክር ሚዛን ላይ ከባድ ከሆነ ጀነት ውስጥ ተምር ካስተከለልን ጀነት መግባታችንን አላረጋገጥንምን

◆ላኢላህ ኢለላህ አልመሊኩል ሀቁል ሙቢን

➥ ይህን ዚክር ያለ ሰው 2 ሽልማት አለው 1 በቀብሩ ወስጥ አይፈራም ሌሎቹ ሲፈሩ እሱ አይፈራም 2 ጀነት ከሚገቡት ሰዎች መጀመሪያ ሰፍ ላይ ነው የጀነትን በር መክፈቻ ከሚይዙት!! ሱብሀነላህ! ወላሂ ትልክ ዚክር

◆ላኢላህ ኢለላህ ወህደሁ ላሸሪከለህ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምድ ወሁወ አላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር ሱብሀነላህ ወልሀምዱሊላህ ወላኢላህ ኢለላህ ወላሁ አክበር

➥ይህንን ዚክር ለፈጅር ሰላት ከእንቅልፍህ እንደነቃህ ፍራሽህ ላይ ሆነህ ካልክ ከሰገድክ ሰላትህ ተቀባይ እንደሆነ እና ዱአ ካደረክ ዱአህም ተቀባይነት እንዳለው ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ቃል ተገብቶልሀል

◆ አልሀምዱሊላህ ሀምደን ከሲረን ጦይበን ሙባረከን ፊህ ከማ ዩሂቡ ረቡና ወየርዳ አዩህመደ ወየንበጊ ለህ

➥ ይህ ዚክር ደሞ አንድ ሰው ወደ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) መጣና አሰላሙ አለይኩም አለ ነብያችንም ሰላምታ መለሱ ከዛ ይህ ሰው ይህንን ዚክር አለ ከዛ ነብያችን ምንድነው ያልከው አሉት ከዛ ደገመላቸው ከዛም ነብያችን አንተ ይህንን ዚክር ስትል ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ 10 መላኢካዎች እንዴት እንደሚፅፉት አደናግሯቸው እርስ በርስ እየተነጋገሩ አየሁ ከዛም አላህ (ሱ.ወ) ባሪያዬ እንዳለው አርጋችሁ ሳፋለት ብሎ አዘዘ

◆አላሁ አክበሩ ከቢራ ወልሀምዱሊላሂ ከሲራ ወሱብሀነላሂ ቡክረተን ወአሲላ

➥ ይህንን ዚክር ሰላት እንደጀመረ አላሁ አክበር ብለን ሰላት ውስጥ እንደገባን ይህንን ዚክር እንበል ከዛ ፋቲሀን (አልሀምዱን) እንቅራ ይህን ያደረገ ሰው የጀነት በሮች ይከፈቱለታል ሰላቱም ተቀባይ ነው ብለዋል ረሱል (ሰ.ዐ.ወ)

◆ሱረቱል ኢኽላስ (ቁልሁወላሁ አሀድ)

➥ሱረቱል ኢኽላስን 10 ጊዜ የቀራ አላህ በጀነት ውስጥ ቤት ይገነባለታል

◆አላሁመ ኢኒ ዘለምቱ ነፍሲ ዙልመን ከሲረን ወከቢራ ወላ የግፊሩ ዙኑበ ኢላ አንት ፈግፊር ሊ መግፊረተን ሚን ኢንዲክ የወርሀምኒ ኢነክ አንተል ገፉሩ ረሂም

➥ የህንን ዱአ ያለ ሰው አላህ (ሱ.ወ) ይገረምለታል ስለዚህ ሁሌም ምህረትን በዚ ዱአ እንጠይቀው

◆አላሁመ ረበ ሀዚሂ ዳእወቲ ታማ ወሰላቲል ቃኢማ አቲ ሙህመደን አልወሲለተ ወልፈዲላ ወብኣስሁ መቃመን መህሙደኒለዚ ወአድተህ ኢነክ ላቱኽሊፋል ሚአድ

➥ይህንን ዚክር አዛን ከተደሰገ በኋላ ያለ ሰው በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) አማላጅነት ጀነት ይገባል

◆ላኢላህ ኢለላህ ወላሁ አክበር ወላህውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢለህ

➥ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል ይህን ዚክር ያለ ሁሉም ወንጀሉ ይማርለታል ሱብሀነላህ!

◆ላኢላህ ኢላ አንት ሱብሀነክ ኢኒ ኩንቱ ሚነ ዚሊሚን

➥ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል ይህንን ዱአ ብሎ ከዛ አላህ የፈለገውን ቢጠይቅ ይሰጠዋል ብለዋል ይህዱአ የተገኘው ከነብዩላህ ዚኑን በአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ ሆኖ ያደረገው ዱአ ነበር

◆ያዘል ጀላሊ ወልኢክራም ያ ሀዩ ያቀዩም

➥አንድ ሰው ይህንን ዚክር ብሎ ከዛ ዱአ ካደረገ አላህ ዱአውን ተቀብሎታል እና ይደሰት ብለዋል ረሱል (ሰ.ዐ.ወ)

◆ያ አርህመራሂሚን ያ አርህመራሂሚን ያ አርህመራሂሚን

➥አንድ ሰው ይህን ዚክር ማለትም ያ አርህመራሂሚን የሚለውን 3 ጊዜ ብሎ ከዛ ዱአ ካደረገ ለዛ ለሰው የተመደበለት መላኢካ አብሽር በርግጥም አላህ ተቀብሎሀል ብሎ ያበስረዋል ብለዋል ረሱል (ሰ.ዐ.ወ)

◆አላሁመ አንተ ረቢ ላኢላህ ኢላ አንት ኸለቅተኒ ወአና አብዱክ ወአና አላ አህዲክ ወወእዲክ መስተጣእት አብኡ ለክ ቢኒእመቲክ አለይ ወአቡኡ ቢዘንቢ ፈግፊር ሊ ፈኢነሁ ላ የግፊሩ ዙኑብ ኢላ አንት

➥ ይህንን ዱአ ፈጅር ማለትም ሱብሂ ላይ ብሎት እስከመግሪብ ባለው ጊዜ ከሞተ እንዲሁም መግሪብ ላይ ብሎት እስከ ፈጅር ወይም እስከ ሱብሂ ባለው ጊዜ ላይ ከሞተ የጀነት ነው እንደው አይሆንም እንጂ ይህ ሰው ጀሀነም ነው የምፈልገው ቢል እንኳን በግዴታው ጀነት ይገባል!!

◆ አስተግፊሩላህል አዚም አለዚ ላኢላህ ኢላ ሁወል ሀዩል ቀዩም ወአቱቡ ኢለይህ

➥ ይንን ዱአ ያለ ከጦር ሜዳ ቢሸሽ እንኳን ወንጀሉ ይማርለታል

◆ ቢስሚላሂ ለዚ ላየዱሩ ማላ ኢስሚሂ ሸይኡን ፊል አርዲ ወላ ፊሰማኢ ወሁወሰሚኡል አሊም

➥ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል ይህንን ዚክር ማታ ሲተኛ እና ሱብሂ ለፈጅር ሲነሳ 3 ጊዜ ካለው ድንገተኛ በላእ (ችግር) አይገጥመውም ከሲህርም መጠበቂያ ይሆናል አንድ ነገር ሲህር እንዳለው እያወቃችሀ ይህን ዚክር ብላችሁ ብትነኩት ወይም ብትረግጡት ምንም አትሆኑም

ጠቃሚ ነጥብ :- ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል የአሹራን ቀን የፆመ ሰው የአንድ አመት ወንጀሉ ይማርለታል ሱብሀነላህ!

ጠቃሚ ነጥብ :- (አላሁመ ኢኒ አስአሉክ ሁስነል ኻቲማ), (አላሁመርዙቅኒ ተውበተን ነሱሀተን ቀብለል መውት) , (አላሁመ ያሙቀሊበል ቁሉብ ሰቢት ቀልቢ አላ ዲኒክ) ሱጁድ ላይ ሊረሱ የማይገቡ 3 ዱአዎች ናቸው

ጠቃሚ ነጥብ :- ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል ሙአዚኑ አዛን ሲያደርግ ሙአዚኑ የሚለውን አብሮ ተከትሎ ያለ ከዛ ሙአዚኑ ኸየ አለሰላት , ኸየ አለልፈላህ የሚለው ላይ ላህውለ ወላቁወተ ኢላ ቢላህ ያለ ሰው ጀነት ይገባል

ጠቃሚ ነጥብ :- ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል የሱብሂ ሰላትን በጀመአ የሰገደ (ለሴት ልጅ እቤቷ) ከዛ ፀሀይ እስክትወጣ ድረስ ዚክር እያደረገ ፀሀይ ከወጣች በኋላ ሁለት ረከአ የሰገደ ሙሉ ሀጅ እና ኡምራ እንዳደረገ ይያዛለታል ያቺ የምንሰግዳት ሁለት ረከኣ ሰላተዱህ ትባላለች ልክ ፀሀይ ወጣ እንዳለች እስከ ዝሁር

ከመግባቱ በፊት ትንሽ ቀደም ብሎ ያለውን ግዜ ትይዛለች ስለዚህ ሱብሂን ከሰገድን በኋላ ፀሀይ እስከምትወጣ ዚክር በማድረግ ፀሀይ እንደወጣች ሁለት ረከኣ በመስገድ ይህንን ታላቅ አጅር ያግኙ በመሆኑም ወንዶች መስጊድ ጀመአ ሰግዳቹህ ሴቶች ደሞ እቤታችሁ ትችላላችሁ

ጠቃሚ ነጥብ :- አሁን አንድ የሞተ ሰው እንደገና ወደ ዱንያ ቢመለስ ወላሂ ወደ ቤተሰቦቹ አይሄድም ነበር ስለ ሀብቱም አይጠይቅም ሚስቱ አገባች ወይስ አላገባች አይልም ልጆቹም ትዝ አይሉትም ግን ይህቺን ዚክር ይል ነበር (ሱብሀነላህ ወልሀምዱሊላህ ወላሂላህ ኢለላህ ወላሁአክበስ) እነዚህ 4 ቃላቶች አላህ ዘንድ በጣም ተወዳጅ ናቸው ስለዚህ እኛም በዚህ ዚክር ላይ እንበራታ

ጠቃሚ ነጥብ :- ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል በምሽት እና በለሊት ወደ መስጅም የመመላለሱን ፈዳኢል (ትሩፋት) ብታውቁ ኖሮ በእንብርክካችሁ ቢሆን እንኳን ትሄዱ ነበር ሱብሀነላህ

ጠቃሚ ነጥብ :- አንዲት ሴት ወደ ነብዩላህ ሙሳ ትመጣና ተውበት ማድረግ እፈልጋለሁ ትለዋለች እሱም ምንድነው የሰራሽው አላት እሷም ከዚና አርግዤ ልጄን ገድሌዋለሁ እና መቶበት እፈልጋለሁ አለችው ሙሳ ተናዶ በመጮህ ውጪ!! ብሎ አባረራት ከዛ ልቧ ተሰብሮ ሄደች ደግማ በሌላ ቀን መጣች አሁንም አባረራት ለ 3 ተኛ ጊዜ ደግማ መጣች አሁንም በቁጣ አባረራት ከዛ አላህም(ሰ.ወ) ለምን ተውበተኛዋን መለስካት አለው ሙሳን ከሷ የበለጠ መጥፎ ሰው እንዳለ አታቅም እንዴ አለው ሙሳም ማን ከዚች ሴትዮ በላይ መጥፎ አለ ዚና የሰራች ከዚና ያረገዘች ያም አልበቃ ብሎ ልጇን የገደለች ናት ብሎ መለሰ አላህም(ሱ.ወ) ከሷ በላይ መጥፎ ሰው ማለት ሰላት የማይሰግድ ነው ሰላት የማይሰግድ ሰው እኔ ዘንድ ከገዳይ ከደፋሪ ከዝሙተኛ ከሀሜተኛ በላይ ነው!!! ስለዚህ ወንድም እህቶቼ ይህን እያወቅን ለምን አንሰግድም
ጠቃሚ ነጥብ :- አንድ ሰው ሁለት ሰዎችን በትዳር ለማጣመር ሲል ለተናገራቸው ለእያንዳንዷ ቃላት ለተራመዳቸው ለእያንዳንዷ እርምጃ ለሊቱን ቆሞ እንደሰገደ እና ቀኑን ፆመኛ እንደሆነ ተደርጎ ይያዝለታል ወላሂ ትልቅ አጅር ነው

ጠቃሚ ነጥብ :- ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል የአረፋን ፆም የፆመ ሰው ያለፈውን አመት እና ወደፊት የሚመጣው አመት ወንጀሉ ይማርለታል!! ሱብሀነላህ!!

ጠቃሚ ነጥብ :- ኢልምን ለመማር (ቂርአት ለመቅራት) አስቦ ወደ መስጅድ የሄደ ሰው ሀጅ እንዳደረገ ይያዝለታል ሱብሀነላህ ወላሂ ታላቅ ጌታ አለን

ጠቃሚ ነጥብ :- የውመል ቂያማ በፍርዱ ቀን ወደ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ቅርብ የምንሆነው በየቀኑ በርሳቸው ላይ በምናወርደው ሰለዋት ልክ ነው እና እህት ወንድሞቼ በየቀኑ በቻልነው መጠን በነብያችን ላይ ሰለዋት እናውርድ መቶም ሁለትመቶም አንድሺም ብቻ የቻልነውን ግን ቁጥሩን ባበዛነው ቁጥር ይበልጥ ወደ ነብያችን ቅርብ እንሆናለን በህልማችንም ልናያቸው እንችላለን እንዲሁም ነብያችንን ናፍቀን ሶስት ሰለዋት ካወረድን አላህ ወንደላችንን የምርልናል በጭንቅ ሰአት እርሳቸው ላይ ሰለዋት ብናወርድ ጭንቅ ሀሳብ መከራ ችግር ይወገዳል

ዱአ ተቀባይ የሚሆንበት ጊዜያቶች

1, ዶሮ ሲጮህ ዱአ አድርጉ ምክንያቱም ዶሮ መላይካ ሲያይ ነውና የሚጮኸው ነብያችንም ዶሮ ሲጮህ ከሰማችሁ ዱአ አድርጉ ብለዋል

2, በአዛን እና በኢቃም መካከል ዱአ አድርጉ ምክንያቱም ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በአዛን እና በኢቃም መካከል የሚደረግ ዱአ ተቀባይ ነው ስላሉ

3, የለሊቱ አንድ ሶስተኛ ላይ ዱአ አድርጉ ይሄም ሱብሂ ከመድረሱ ከሁለት ወይም ከአንድ ሰአት በፊት ማለት ነው ምክንያቱም አላህ(ሱ.ወ- ወደዱንያ ሰማይ ይወርድና ማነው የሚጠይቀኝ የምሰጠው ማነው ምህረት የሚጠይቀኝ የምምረው ስለሚል

4, ሱጁድ ላይ ስትሆኑ ዱአ አድርጉም ምክንያቱም ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል አንድ ባሪያ ወደ ጌታው ቅርብ የሚሆነው ሱጁድ ላይ ነው

5, በጁምአ ቀን ዱአ አድርጉ ምክንያቱም በጁምአ ቀን አንድ የማትታወቅ ጊዜ አለች አላህ ያቺን ጊዜ ካጋጠመህ ዱአህ ተቀባይ ነው

6, ሰላት ላይ የመጨረሻውን ተሸሁድ እንደጨረስን ከማሰላመታችን በፊት የፈለግነውም ዱአ እናድርግ ከዛ እናሰላምታለን

7, መልካም ስራ ከሰራችሁ በኋላ ዱአ አድርጉ ምክንያቱም አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ላይ እንዲህ ይላል በጥሩ ስላ ላይ ይታገላሉ ከዛም ዱአ ያደርጋሉ

8, ጉዞ ላይ ስትሆኑ ዱአ አድርጉ ምክንያቱም ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል የመንገደኛ ዱአ አይመለስም

9, ያመን ልናፈጥር ስንል ይሌ ማለት ሳናፈጥር ወይም ምግብ ሳንጠቀም ከዛ ዲአችንን ካደረግን በኋላ ማፍጠር ጊዜው መግሪብ አዛን ከመደሰጉ በፊት ትንሽ ቀደም ብሎ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል የያመኛ ዱአ አይመለስም

ከመተኛታችን በፊት መደረግ ያለባቸው ነገሮች

1, ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) አልይን እንዲህ አሉት አንተ አልይ በአንድ ለሊት 4000 ዲናር ሰደቃ አውጣ ቁርአንን አክትም የጀነትን ዋጋዋን ክፈል ሁለት የተጣሉ ሰዎችን አስታርቅ እና ሀጅ አርግ አሉት አልይም ያረሱለላህ ይህንን ሁላ በአንድ ለሊት እንዴት አደርጋለሁ አላቸው ረሱልም ከመተኛትህ በፊት ፋቲሀን 4 ጊዜ ቅሬ 4000 ዲናር ሰደቃ አወጣህ ማለት ነው 3 ጊዜ ቁልሁወላሁ አህድን ከቀራህ ቁርአን አኽተምክ ማለት ነው 3 ጊዜ(ላህውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ) ካልክ የጀነትን ዋጋዋን ከፈልክ ማለት ነው 10 ጊዜ (አስተግፊሩላህል አዚም) ካልክ ሁለት ሰዎችን እንዳስታረክ ያክል ነው 4 ጊዜ ሸህዳ ካደረክ ማለትም አሸህዱ አላሂላህ ኢለላህ ወአሸህዱ አነ ሙህመደን ረሱሉላህ ሀጅ አደረክ ማለት ነው

2, አያተል ኩርሲይ መቅራት ምክንያቱም እስክ ሱብሂ ድረስ በአላህ ጥበቃ ውስጥ እንሆናለን

3, ሱረቱል ሙልኩ (ተባረክን) መቅራት ምክንያቱም ከቀብር ቅጣት ይጠብቀናል

4, ይህንን ዚክር ማለት (ላኢላህ ኢለላህ ወላሁ አክበር ላኢላህ ኢለላህ ወህደሀ ላኢላህ ኢለላህ ወላ ሸሪክ ለህ ላሊላህ ኢለላህ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምድ ላኢላህ ኢለላህ ወላ ሀውለ ወላቁወተ ኢላ ቢላህ) አንድ ሰው ይህንን ዚክር ብሎ በዛን ለሊት ወይም በዛን ቀን ወይም በዛን ወር ከሞተ የጀነት ነው ረሱል (ሰ.ዐ.ወ)

ከሰላት በኋላ መደረግ ያለባቸው ነገሮች

1, ቶሎ አለመነሳት መቀመጥ ምክንያቱም ሰግደን ስንጨርስ ውዱእ እስካልፈታን እና ከተቀመጥንበት እስካልተነሳን ድረስ መላኢካዎች አላህን ምህረት ይጠይቁልናል

2, (አላሁመ አንተ ሰላም ወሚንከሰላም ተባረክተ ያዘል ጀላሊ ወል ኢክራም) ማለት

3, (ላኢላህ ኢለላህ ወህደሁ ላ ሸሪከለህ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምድ)ማለት ግን መግሪብ እና ሱብሂ ሰላት ላይ 10 ጊዜ ማለት ሌላው ሰላት ላይ ግን 1 ጊዜ

4, (አላሁመ ላሚኒአ ሊማ አእጠይት ወላ ሙእጢየ ሊማ መናእት ወላ የንፉኡ ዙልጀዱ ሚንከል ጀድ) ማለት

5, (አየተል ኩርሲይ መቅራት አላሁ ላኢላህ ኢላሁወል ሀዩል ቀዩም የሚለውን ከቁርአን ሙሉ እንህፍዝ) ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል በእንዳንዱ ግዴታ ሰላት ጀሮባ አየተል ኩርስይ የቀራ ሰው ጀነት ለመግባት ሞት ብቻ ነው የሚያግደው

6, (ሱህነላህ)33 ጊዜ (አልሀምዱሊላህ)33 ጊዜ (አላሁ አክበር) 33 ጊዜ ባጠቃላይ 99 ይሆናሉ ከዛ ላኢላህ ኢለላህ ወህደሁ ላ ሸሪከለህ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምድ 1 ጊዜ ብለን 100 ከሞላን ወንጀላችን የባህር አረፋ ያክል ቢበዛ ይማርልናል ረሱል (ሰ.ዐ.ወ)

7, ተአውዞችን መቅራት ማለትም ቁልሁወላሁ አህድን እና ሁለቱ ቁል አኡዞችን መቅራት ግን መግሪብ እና ሱብሂ ላይ ሶሰት ጊዜ ሌሎቹ ሰላቶች ላይ አንዳን ጊዜ ይህን የማድረግ ጥቅሙ ሁሌ በአላህ ጥበቃ ውስጥ ነን ሲህር ለራሱ ምንም አያደርገንም

8, በመጨረሻም (አላሁመ አኢኒ አላ ዚክሪከ ወሹክሪከ ወሁስኒ ኢባደቲክ) ሁሌም ከግዴታ ሰላቶች በኋላ እነዚህን እንተግብር

ኢንሻ አላህ ባነበብነው የምንጠቀም ያድርገን